# የፌደራል ኢሚግሬሽን ጽሕፈት ቤት የወሰነዉን ውሳኔ በመቃወም እንዴት ተደርጎ ነው ይግባኝ የሚባለው?

**ከፌደራል ኢሚግሬሽን ጽሕፈት ቤት (BFM)**
**የጥገኝነት ማመልከቻዎ አሉታዊ ዉሳኔ ተወስኖ ደርሶዎታል?**

ምክር ከፈለጉ ወይም ይግባኝ መጻፍ ከፈለጉ፣ ወዲያው ኣጠገብዎ ወደሚገኝ/ምትገኝ ጠበቃ ወይም የሕጋዊ ምክር ሰጪ „Rechtsberatungsstelle" ያምሩ። ይግባኝ የሚሉበት የጊዜ ገደብ ሳያልቅ፣ እስር ቤት ሊገቡ ስለሚችሉ፣ በጊዜው እርምጃ ይዉሰዱ። የሕጋዊ ምክር ማደራጀት ካልቻሉና ወዲያው እርምጃ መዉሰድ ካለብዎት፣ ይሄ መመሪያ ይረዳዎታል። መመሪያዉ የመነጨው ከስዊዘርላንድ የስደተኞች የእርዳታ ድርጅት SFH (www.osar.ch) ነው። ድርጅቱ ከመንግስት ነጻ የሆነ፣ ጥገኝነት ላመለከቱና ለስደተኞች መብት የሚከራከር ድርጅት ነው። መመሪያዉን በትክክል ኣንብበው ይከተሉት።

## 1. ማወቅ ያለብዎት ጉዳይ

**→ ኣንድ ጊዜ ብቻ ነው ይግባኝ ማለት የሚችሉት**

የሚመለከተው የፌደራል ኣስተዳደር ፍርድ ቤት (Bundesverwaltungsgericht) ነው። ይህ ፍርድ ቤት የጥገኝነት ማጣሪያን በሚመለከት ከፍተኛው ፍርድ ቤት ነው። ዉሳኔዉም የመጨረሻ ነው። ኣድራሻው እንደሚከተለው ነው።

Bundesverwaltungsgericht
Postfach, CH-3000 Bern 14
Telefon +41 (0)58 705 26 26, Fax +41 (0) 58 705 29 80

**→ የጊዜ ገደብ ኢያሳልፉ**

**የጊዜ ገደብን የሚጠቅስ ኢንፎርሜሽን በዉሳኔው መጨረሻ ላይ፣ የሕጋዊ ማብራሪያ** „Rechtsmittelbelehrung" ከሚል ኣርእስት ስር ያለዉን ይገንዘቡ። እዛ ላይ ይግባኝ ለማለት ምን ያህል ጊዜ እንዳለዎት ተጽፏል። የተለያዩ የዉሳኔ ኣይነታት ኣሉ። ከዉሳኔዎቹ ሁለቱ እነዚህ ናቸው።

1. **የጥገኝነት ማመልከቻዎ ተቀባይነት ኣላገኘም።** ዉሳኔው ከደረሰ **ሰላሳ ቀናት** ሳይሞላ ይግባ'ኙን መላክ ኣለብዎት። ቅዳሜ፣ እሁድና የበዓል ቀናትም ይቆጠራሉ።
2. **የጥገኝነት ማመልከቻዎ ታማኝነት ኣላገኘም።** ይህ ማለት ማመልከቻዎ ብቁ ምክንያት የሌለው ወይም ሕገወጥ ነው ማለት ነው። **ኣምስት የስራ ቀናት** ባልሞላ ጊዜ ዉስጥ ይግባኝ ማለት ኣለብዎት። ቅዳሜ፣ እሁድና የዕረፍት ቀናት ቁጥር ዉስጥ ኣይገቡም። ወደ ሌላ የኤዉሮጳ ኣገር ለሚመለሱ፣ ሊያዉቁት የሚገባ ልዩ ነገር፤ ይግባ'ኙ የመመለስን ጊዜ ኣያጓትትም።

ጊዜ ላለማጥፋት፣ ይግባ'ኙን ኣስቀድመው በፋክስ፣ ቀጥለውም ኦሪጂናሉን በደብዳቤ ይላኩ።

## 2. መዝገብ ማዘዝ

የፌደራል ጽሕፈት ቤቱ ዉሳኔ ምን ተሞርክዞ የርስዎን ማመልከቻ እንዳልተቀበለ የሚገልጽ መዝገቦች በሙሉ በጅዎ ካሉ፣ ይግባኝ የሚሉበትን ምክንያቶች ለመጥቀስ ይቀልዎታል። ከፌደራል የኢሚግሬሽን ጽሕፈት ቤት (BFM) ማህደርዎ ያልተላከ ከሆነ፣ ማህደርዎ ባፋጥኝ እንዲላክልዎት ይዘዙ።

**የመዝገብ ማየት ማመልከቻ** „Akteneinsichtsgesuch“ **ለማቅረብ ፎርሙላ** A (vorlage A) **ይጠቀሙ። እዚህ ፎርሙላ ወስጥ ✍ ምልክት ባለበት ቦታ ላይ ይጻፉ።**

**→ እያንዳንዱን ፎርሙላዉ ዉስጥ ያሉትን ነጥቦች ይሙሉ።**

| | |
|---|---|
| 1 | ማንነትዎንና የአሁኑ አድራሻዎ ( የቤተሰብ ስም፣ መጠርያ ስም፣ የ (BFM) ዉሳኔ የሚመለከታቸው ግለሰቦች የትዉልድ ዕለት፣ ጎደና፣ የፖስታ ቁጥር ኮድና(PLZ)/ ከተማ) |
| 2 | ቦታ፣ ዕለት |
| 3 | N- ቁጥር ( ባለ ስድስት አሃዝ፣ የ (BFM) ዉሳኔ እላይ ብስተ ግራ በኩል ኣለ።) |
| 4 | BFM የወሰነበት ዕለት ( በዉሳኔው እላይ በስተ ግራ በኩል ኣለ።) |
| 5 | የመዝገብ ማየት ማመልከቻዉን „Akteneinsichtsgesuch“ ይፈርሙበት። |
| 6 | ፎርሙላዉን በተመዘገበ ደብዳቤ „Einschreiben“ ወደ Bundesamt für Migration, Quellenweg 6, 3003 Bern-Wabern ይላኩት። |

**ከጥቂት ቀናት በኋላ የቃለ መጠይቅ ፕሮቶኮል ኮፒ፣ ምናልባትም ተጨማሪ ማህደሮች ይደርስዎታል። ለዚሁ ደብዳቤ ገንዘብ ኣይከፍሉም።**

## 3. ይግባኝ ማዘጋጀት

**→ የሶሺያል እርዳታ ያገኛሉን?**

**የሶሺያል እርዳታ ሰጪ ቢሮ** „Sozialhilfestelle“ **ማረጋገጫ እንዲሰጥዎት ይጠይቁ። ማረጋገጫዉን ከይግባኙ ጋር ያያይዙት። ማረጋገጫዉ የጊዜ ገደቡ ካለፈ በኋላ ከደረሰዎት፣ ይግባኙን ኣስቀድመው ልከው፣ ማረጋገጫው እንደደረሰዎት ባፋጣኝ ይላኩት።**

**→የፌደራል ኢሚግሬሽን ጽሕፈት ቤት** (BFM) **ዉሳኔን ያስተርጉሙ**

**የፌደራል ኢሚግሬሽን ጽሕፈት ቤት** (BFM) **እርስዎን ላለመቀበል ያቀረባቸዉን ምክንያቶች ያስታዉሱ። ይግባኙ ላይ እነዚህን ምክንያቶች በሚመለከት ሃሳብዎን ይግለጹ።**

**→ማስረጃዎች ያቅርቡ**

**ከይግባኙ ጋር፣ እስካሁን ለስዊዘርላንድ ጽሕፈት ቤቶች ያልሰጡትን፣ ለጉዳይዎ ጠቃሚ የሆኑ ማስረጃዎችን በሙሉ ይላኩ።** (**ለምሳሌ፡ የሓኪም የምስክር ወረቀት፣ የእስር ትእዛዝ፣ ፍርድ ወ.ዘ.ተ.**)**። ዶኩሜንቶቹን በጊዜው ያሰናዱ።**

## 4. ይግባኝ መጻፍ

**ይግባኙን በጀርመንኛ፣ በፈረንሳይኛ ወይም በጣልያንኛ ማቅረብ ይቻላል። ምናልባት እርስዎ በመጻፍ ሊረዳዎት የሚችል ሰው ያዉቁ ይሆን? እርስዎም የይግባኝ ፎርሙላ** „B“ „Beschwerdevorlage B“ **መጠቀም ይችላሉ። ዋናዎቹ ማመልከቻዎች እዛ ታትመዋል። እርስዎ ፎርሙላዉን የግልዎን ሁኔታን እንደሚመለከት መሙላት ኣለብዎት። ፎርሙላው ላይ ✍ ምልክት ባለበት ቦታ ይጻፉ። ለጽሑፉ ቦታው ካልበቃዎት፣ ተጨማሪ ወረቀት ይጠቀሙ።**

**→እያንዳንዱን የይግባኝ ፎርሙላዉ „Beschwerdevorlage B“ ዉስጥ ያሉትን ነጥቦች ይሙሉ።**

| | |
|---|---|
| 7 | ቦታ፣ ዕለት |
| 8 | ማንነትዎንና አድራሻዎ ( የቤተሰብ ስም፣ መጠርያ ስም፣ የትዉልድ ዕለት፣ ጎደና፣ የፖስታ ቁጥር ኮድና(PLZ)/ ከተማ። በ (BFM) ዉሳኔ ስማቸው የተጠቀሱትን ግለሰቦች ስም ዝርዝራቸዉን ይጻፉ።) |
| 9 | BFM የወሰነበት ዕለት ( በዉሳኔው እላይ በስተ ግራ በኩል ኣለ) |
| 10 | N- ቁጥር ( ባለ ስድስት ኣሃዝ፣ የ (BFM) ዉሳኔ እላይ ብስተ ግራ በኩል ኣለ።) |

<table>
<tr>
<td>11</td>
<td>ይህ የይግባኙ ዋናዉ ክፍል ነው። እርስዎ ለምን የ (BFM) ዉሳኔን እንደሚቃወሙና ለምን ስዊዘርላንድ ዉስጥ መቅረት እንደሚፈልጉ፣ በዝርዝር ምክንያትዎን ይግለጹ። ለሚጽፉት ቦታው ካልበቃዎት፣ ተጨማሪ ወረቀት ይጠቀሙ። ያስታዉሱ።<br>• (BFM) ያቀረባቸውን ምክንያቶች እያንዳንዱን ነጥብ ኣበጥረው መልስ ይስጡበት።<br>• የ (BFM) ዉሳኔ እርስዎ ያቀረቡት ማብራርያ የማይታመን ነው ብሎ ይሆን? እንደዛ ከሆነ ያንን የሚያፈርስ ሓሳቦችን ይግለጹ። የተፈጠረዉን ያለመግባባትን ለማስረዳትና ግልጽ የሆኑ የተምታቱ ምክንያቶችን ለማስረዳት ሞክሩ።<br>• ኣሁን ወደ ኣገርዎ ቢመለሱ ምን ሊያጋጥምዎት ይችላል? ማን፣ መቸ፣ ለምን እርስዎን እንደሚከታተሉ በትክክል ያስረዱ፡<br>• በርስዎ ላይ ክትትል እንደሚደረግ ማስረጃ ቢኖርዎት ጥሩ ነው። እስካሁን ድረስ ያልሰጡትን ማስረጃዎቹን በሙሉ ያቅርቡ ( ለምሳሌ፡ የእስር ዉሳኔ፣ የፍርድ ቤት ዉሳኔ፣ የሓኪም ምስክር ወረቀት፣ የጋዜጣ ጽሑፍ ወ.ዘ.ተ.) ትርጉማቸዉንም ይግለጹ።<br><br>ኣምስት ቀናት ብቻ ይግባኝ የማለት ገደብ ላላቸው ተጨማሪ<br>• የመታወቂያ ወረቀት ወይም ፓስፖርት ያልሰጡ ከሆነ፣ ለምን እንዳልሰጡ በትክክል ያስረዱ።<br>• ባለስልጣኖቹ በርስዎ ጉዳይ፣ ተጨማሪ የሆነ ሊረጋገጥላቸው የሚፈልጉት ክስተት ካለ፣ የተከሰተዉን ይጻፉ( ለምሳሌ፡ የተደረገ ነገር፣ ከተማዎ ዉስጥ ያለ የፖለቲካ ሁኔታ)።<br>• (BFM) እርስዎን ወደነበሩበት ሶስተኛው ኣገር ሊልክ የፈለገ እንደሆን፣ ለምን ወደዛ መሄድ እንደሌለብዎት ያብራሩ። ( ለምሳሌ፡ ከሶስተኛው ኣገር በቀጥታ ወደ ትዉልድ ኣገርዎ እንዳይላኩ ፍርሃት እንዳለብዎት፣ ስዊዘርላንድ ዉስጥ የቅርብ የቤተሰብ ኣባል ወይም ዘመድ እንዳለዎት)<br>ወደ ኤዉሮጳ ኣገር ፣ ኖርወይ ወይም ወደ ኣይስላንድ ስለ መመለስ። ሊያዉቁት የሚገባ፡ ይግባኙ የመመለስን ጊዜ ኣያጓትትም።<br>ይህ ማለት፣ እርስዎ የይግባኝ ማመልከቻ ቢያቀርቡም ወደዛ ይላካሉ። እርስዎ ከዚህ በፊት የነበሩበት የኤዉሮጳ ኣገር እርስዎን ለመቀበል ፍቃደኛ ከሆነ፣ ወደዛ ይላካሉ። በይግባኙ ምክንያት መመለሱ እንዲቆይልዎት ይጠይቁ። ይህ የኤዉሮጳ ኣገር፣ ለምን ጉዳየኝ ኣያይልኝም ብለው እንደሚፈሩና በትዉልድ ኣገርዎ ዉስጥ ኣርስዎን ምን ዓይነት ኢሰብኣዊ ወይም የሚያዋርድ ጉዳይ እንደሚያስፈራዎት ይግለጹ።</td>
<td>በስዊዘርላንድ የጥገኝነት ሕግ መሰረት ስደተኞች ጥገኝነት ሊያገኙ ይችላሉ።<br><br>የጥገኝነት ሕግ ኣንቀጽ 3<br><br>< ስደተኞች የሚባሉት፣ በትዉልድ ኣገራቸው ወይም መጨረሻ ይኖሩበት በነበረው ኣገር ዉስጥ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በዜግነት፣ የኣንድ የሕብረተሰብ ክፍል ኣባል በመሆናቸው ወይም በፖለቲካዊ ኣመለካከታቸው ምክንያት ለሚጎዱ ሁኔታት የተዳረጉ ወይም ለተመሳሳይ ጉዳቶች እንደሚዳረጉ ተጨባጭ የሆነ ስጋት ያላቸው እንደሆነ ነው። የሚጎዱ ሁኔታዎች ተብለው የሚጠቀሱት፣ ለኣካልና ለህይወት ጉዳት መዳረግ፣ ነጻነትን የማጣት ስጋት ከዛም ኣልፎ ለከባድ የኣእምሮ ጭንቀት የሚዳርጉ ጫናዎች በግለሰብ ላይ ሲደርስ ነው። ሴቶችን ብቻ የሚመለከቱ የስደት ምክንያቶች ግምት ዉስጥ ይገባሉ።></td>
</tr>
<tr>
<td>12</td>
<td colspan="2">የጥገኝነት መብት ካልተሰጠዎት፣ ነገር ግን እርስዎን ከዚህ ኣገር ለማስወጣት የማይቻል ከሆነ፣ ስዊዘርላንድ ዉስጥ ጊዜያዊ ተቀባይነት (F-የመታወቂያ ወረቀት) ሊሰጥዎት ይችላል። እርስዎን ወደ ትውልድ ኣገርዎ መላክ ኢሰብኣዊ ተግባር ሊሆን ከቻለ፣ እርስዎን ከዚህ ኣገር ማስወጣት ኣይቻልም። እንደዚህ የሚሆን ለምሳሌ፣ እርስዎ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ለተለዩ ሌሎች ጭብጥ ለሆኑና ለሚያሰጉ ሁኔታዎች የሚዳረጉ ምክንያቶች ካሉ ነው።<br>ወደ ትውልድ ኣገርዎ እናዳይመለሱ የሚረዱ፣ እስካሁን ያልተጠቀሱ ሌሎች ምክንያቶችን ዘርዝረው ያቅርቡ። ኣንዳንድ ምክንያቶች ለመጥቀስ፤</td>
</tr>
<tr>
<td></td>
<td colspan="2">• ለጽኑ በሽታዎ፣ ስዊዘርላንድ ዉስጥ ብቻ የሕክምና እርዳታ ማግኘት የሚችሉ ከሆነ፤ በጤንነትዎ ምክንያት፣ በርስዎ ላይ ወደ ትውልድ ኣገር የመመለስ እርምጃ መፈጸም፣ ግፍ ነው። ወደ ትውልድ ኣገርዎ ቢመለሱ፣ ምን ዓይነት የጤና ችግር ሊያጋጥምዎት እንደሚችል ይግለጹ፣ ያሁኑን የሐኪም ምስክር ወረቀት ያቅርቡ። የፌደራል ኣስተዳደር ፍርድ ቤት (Bundesverwaltungsgericht) የርስዎን የሕክምና ምርመራ ሪፖርት እንዲያመጣ ይጠይቁ።<br>• የትውልድ ኣገርዎ ውስጥ የርስ በርስ ጦርነት፣ ወይም ባጠቃላይ ጭካኔ የሰፈነበት ሁኔታ ሰፍሯል። ወደ ትውልድ ኣገርዎ መመለስ፣ በርስዎ ላይ ምን ዓይነት ችግር ሊያስከትል እንደሚችል ይግለጹ።<br>• ኣብዛኛው ጊዜ የፌደራል ኢሚግሬሽን ጽሕፈት ቤት (BFM)፣ እርስዎ በትውልድ ኣገርዎ ውስጥ ከለላ ማግኘት ይችላሉ ብሎ ይጠቅሳል። ይህም ማለት፣ እርስዎ በትውልድ ኣገርዎ ውስጥ ከነበሩበት ኣከባቢ የተለየ እርስዎን ወደማያሰጋ ኣከባቢ ሄደው መኖር ይችላሉ ማለት ነው።</td>
</tr>
</table>

| | |
|---|---|
| | ምናልባት እርስዎን ወደ እንደዚህ ዓይነት ኣከባቢ ሂድ ማለቱ ግፍ ሊሆን ይችላልን? የሚቀጥሉት ምክንያቶች ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ።<br>— እዛ ኣከባቢ በገንዘብ እጦት ለመኖር ኣይችሉም (ለምሳሌ፤ ባለዎት የትምህርት ደረጃ ምክንያት፣ በቋንቋ፣ እዛ ኣከባቢ ባለው ሁኔታ ወ.ዘ.ተ. ስራ ሊያገኙ ስለማይችሉ።)<br>— ከለላ ይሰጥዎታል ከሚባለው ኣከባቢ ጋር ምንም ግንኙነት የለዎትም።( እዛ ኣከባቢ ኖረው ኣያዉቁም ወይም በጣም ኣጭር ጊዜ ብቻ ነው የኖሩት፣ ያካባቢዉን ቋንቋ መናገር ኣይችሉም፣ ባካባቢው ዘምድ ይሁን ጓደኛ የለዎትም ወ.ዘ.ተ.)<br>— በዕድሜ፣ በጾታዎ፣ ወይም የቤተሰብዎ ቁጥር በጣም ብዙ በመሆኑ ምክንያት፣ እዛ ኣከባቢ ለመቀመጥ ኣይችሉም። |
| 13 | በመጨረሻው ገጽ ላይ የሚልኩትን ማስረጃዎች በሙሉ ይመዝግቡት። ኦሪጂናል ይላኩ። ኮፒ ኣድርገው ይያዙት። የጥገኝነት ዉሳኔዉን ኮፒ ኣድርገው ማያያዝ ኣለብዎት። እርዳታ የሚሰጥዎት ከሆነም፣ ከርዳታ ሰጪው ማረጋገጫ ወስደው ያያይዙት። **ኣሁን የይግባኙን ወረቀቶች በሙሉ ሁለት ጊዜ ኮፒ ያድርጉ።** |
| 14 | ሶስቱን ግልባጮች በሙሉ ይፈርሙበት። ሁለቱን የይግባኝ ግልባጮች ከሙሉ ወረቀቶቹ ጋር (የ BFM-ዉሳኔ ኮፒ፣ የሶሺያል እርዳታ ማረጋገጫ እና ሌሎቹን ማረጋገጫዎች) በምዝገብ ደብዳቤ „Einschreiben“ ኣድርገው ወደ የፌደራል ኣስተዳደር ፍርድ ቤት Bundesverwaltungsgericht, postfach, 3000 Bern 14 ይላኩ። **የጊዜ ገደቡን ያክብሩ።** |

## 5. ቀጥሎስ ምን ይደረጋል?

ከፌደራል ኣስተዳደር ፍርድ ቤት (Bundesverwaltungsgericht) ደብዳቤ ይደርስዎታል። ይዘቱን ያስተርጉሙትና ኣስፈላጊ ከሆነ ፈጠን ብለው የሚደረገውን ያድርጉ። የተለያዩ መልሶች ኣሉ። ከዚህ ቀጥሎ ዋናዎቹ ብቻ ተዘርዝረዋል።

- ከፌደራል ኣስተዳደር ፍርድ ቤት (Bundesverwaltungsgericht) **ደብዳቤዎ ደርሶናል** „Eingangsbestätigung“ የሚል ደብዳቤ ይደርስዎታል። ፍርዱ እስከሚወሰን ድረስ በስዊዘርላንድ ውስጥ በሕጋዊነት መኖር ይችላሉ። ዉሳኔው ግን ከጥቂት ቀናት በኋላ ሊመጣ ይችላል።
- የፌደራል ኣስተዳደር ፍርድ ቤት (Bundesverwaltungsgericht) ይግባኙ **ከመጀመሪያው ጀምሮ ተስፋ የሌለው እንደሆን** „Zum vornherein aussichtslos“ ለመወሰን ይፈልጋል። ለንደዚህ ዓይነት ጉዳይ ፍርድ ቤቱ ቀብድ እንዲከፈለው ያዛል። ለክፍያውም የጊዜ ገደብ ይሰጣል። ያልከፈሉ እንደሆን ይግባኙ ኣይጣራልዎትም። የከፈሉ እንደሆን ይግባኙ ይጣራልዎታል፣ ለማሸነፍ ያለዎት ዕድል ግን በጣም ዝቅተኛ ነው።
- የፌደራል ኣስተዳደር ፍርድ ቤት (Bundesverwaltungsgericht) በይግባኝ ውስጥ ያለዉን ስህተት እንዲያርሙ በጣም ኣጭር የጊዜ ገደብ ይሰጥዎታል። ፈጠን ብለው የተባለዉን ያድርጉ፣ ኣለበለዚያ ይግባኙ ኣይጣራልዎትም።
- የፌደራል ኣስተዳደር ፍርድ ቤት (Bundesverwaltungsgericht)፣ „BFM“ ላመጣዉ ኣዲስ ግምገማ፣ የርስዎን ሓሳብ እንዲሰጡ እድል ይሰጥዎታል። ሓሳብዎን ለመግልጽ ይሞክሩ።

የፌደራል ኣስተዳደር ፍርድ ቤት (Bundesverwaltungsgericht) ውሳኔ የተለያየ ሊሆን ይችላል። ፍርዱ ኣሉታዊ ከሆነ፣ ስዊዘርላንድን ለቀው መሄድ ኣለብዎት። የፌደራል ኣስተዳደር ፍርድ ቤት ጠቅላላዉን ወደ „BFM“ እንደገና እንዲጣራ ሊመልሰው ይችላል። ፍርዱ ኣዎንታዊ ከሆነ፣ እርስዎ ጥገኝነት ያገኛሉ ወይም ጊዜያዊ መኖሪያ ይሰጥዎታል።

ለይግባኝ ከፌደራል ኣስተዳደር ፍርድ ቤት (Bundesverwaltungsgericht) የሚሰጥ ዉሳኔ በሕጉ የመጨረሻ ነው። ከፍ ወዳለው የፌደራል ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ኣይቻልም። ለበጣም ልዩ ለሆኑ ጉዳዮች ብቻ ናቸው እንደገና ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚችሉት ወይም ይግባኝ ማለት የሚቻለው። ለበለጠ ኢንፎርሜሽን በሕግ ማማከሪያ ቢሮ „Rechtsberatungsstelle“: (http://www.fluechtlingshilfe.ch/hilfe/nuetzliche-adressen) ይጠይቁ።